# ሰሞነኛ (5)

## «የበጎ አድራጎት ስራ ወሰኑ በጎ ተግባር ነው»

## በሎስአንጀለስ የኢትዮጵያ ቆንስላ

## ጀኔራል ጽ/ቤት




**Consulate General of Ethiopia**

**3460 Wilshire Blvd #308**

**Los Angeles, CA 90010**

**Tel: 213 365 6651 Fax: 213 365 6670**

www.ethioconsulate-la.or


**ጥር/2001**

**January /2009**

# የበጎ አድራጎት ስራ  ወሰኑ በጎ ተግባር ነው፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ እንደሁሉም ታዳጊ አገሮች ኢኮኖሚያዊ ዕድገቷ የተሳለጠ እንዲሆን የውጭ ዕርዳታ ማግኘት ይጠቅማታል፡፡ ለልማት የቆመው የኢትዮጵያ መንግስት ከልዩ ልዩ ምንጮች ሀብት በመሰብሰብ በቁልፍ የልማት ተግባራት ላይ እንዲውል አበክሮ ሲሰራ ይታያል፡፡

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከተለያዩ ምንጮች ገንዘብና ንብረቶችን በማሰባሰብ በአገራችን የልማት ተግባራት በመሳተፍ ድህነትን ለማስወገድ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ ሁነኛ አጋር ናቸው፡፡ እነዚህ ድርጅቶች በገንዘብና በንብረት ምንጭነት ብቻ ሳይሆን ከመነሻቸው ካለው የተሻለ የቴክኖሎጂና የዕውቀት ደረጃ አንፃር አዳዲስ ልምዶችን ይዘው ወደ አገራችን መግባት መቻላቸው የጀመርናቸውን የልማት መርሀ - ግብሮች ለማሳለጥና ለማዳበር ይረዳሉ፡፡

የመንግስትና የግል ባለሀብት ትሩፋቶች ሁሉንም የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማት መስኮች ሊሸፈኑ ሰለማይችሉ መንግስታዊ ያልሆኑ የበጎ ሥራ ድርጅቶች በጎደለው በመሙላት የላቀ ሚና አላቸው፡፡

መንግስታዊ ያልሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎችም አውራ ጥቅሞች ቢኖራቸውም በተለያዩ ችግሮች የተተበተቡ መሆናቸው ደግሞ አይካድም፡፡

በአገራችን ከተሰማሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች መካከል አንዳንዶቹ ከውጭ ይዘውት ከሚገቡት ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ ዳጎስ ያለውን ለአስተዳደራዊ ወጪዎች የሚያውሉ መሆናቸው አብዩ ችግር ነው፡፡በሚያዋቅሯቸው ጽ/ቤቶች ውስጥ በሀላፊነት ሆነ በተራ ሰራተኛነት የሚቀጥሯቸው ሰራተኞች  ደሞዝ፣አበልና ጥቅማጥቅም  ግዙፍ በመሆኑ ከሚሰሩት የታለመ አንኳር ስራ ይልቅ የስራ ማስኬጃው እንዲገዝፍ ምክኒያት ሆኗል፡፡አንዳንዶች መያዶች ከውጭ ለሚቀጥሯቸው አማካሪዎች ሆኑ ሀላፊዎች የሚከፍሉት ገንዘብ በተግባር ከሰጡት ሆነ ይሰጡታል ተብሎ ከሚገመተው አስተዋፅኦ ጋር በፍፁም የማይዛመድ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ጥቂቶች ደግሞ በስምምነት ባስቀመጡት የፕሮጀክት የጊዜ ሰሌዳ ምንም ተጨባጭ ተግባር ሳያከናውኑ የመደቡትን ገንዘብ

በአስተዳደራዊ ወጪዎች አንጠፍጥፈው የሚከስሙ መኖራቸው በየጊዜው የሚስተዋል ጉዳይ ነው፡፡

እነዚህ መያዶች በተለያየ ግዜ የሚያሰባስቡት የሰራተኛ ሀይል የግልፅነትና የተጠያቂነት መርሆዎችን መሰረት አድርጎ የተቀጠረ ባለመሆኑ ፣ከቅጥር ፍትሀዊነት (Equal job opportunity) መርህ አኳያ ብዙ ሳንክ እንደሚታይበት በተለያየ ጊዜ በተደረጉ ጥናቶችና በዓመታዊ የመያዶች ግምገማ (evaluation) ወቅት አዘውትሮ የሚታይ ነው፡፡

በጎ አድራጎት ድርጅቶች በአብዛኛው አሰራሮቻቸው ቀልጣፋና አጭር ቢሆንም፣ በብዙ መልኩ ለሙስና የተጋለጡ መሆናቸው ታይቷል፡፡ይህም ከመነሻው የገንዘብ ምንጩና በተግባር ውስጥ በገቡ ፕሮጀክቶች መካከል ያለው ግንኙነት በግልፅነት መርህ ላይ የተመሰረተ አለመሆኑ ፣የሰራተኛ ቅጥራቸው ከሥራ ቅጥር ርዕታዊነት ወጣ ያለ መሆኑና ፣የንብረት ግዢ፣ አወጋገድና አሰራሩ የራሱ የሆነ ለሙስና በር የሚከፍቱ አካሄዶችን የተከተለ እንደነበር የአደባባይ እውነታ ነው፡፡

ከውጭ የሚገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ሌላው ችግር በአገራችን ውስጥ ለኢትዮጵያውያን ብቻ እንደ ዜጋ በተፈቀዱ የፖለቲካ ጉዳዮች ውስጥ ሁነኛ ተዋናይ ሆነው ለመቆም የሚያደርጉት ጥረት ነው፡፡ ይህ አካሄድ ዘመንተኛውን የኒዮ-ሊበራል እሴቶችና አስተሳሰብ መልህቆችን ዋነኛና ብቸኛ ገዢ ሀሳብ ለማድረግ የታለመ ሁለገባዊ እንቅስቃሴ አካል ሲሆን፣ በአመዛኙ በፖለቲካ ጉዳዮች ከዳራቸው (ከወሰናቸው) ውጭ የሚንቀሳቀሱ መያዶች ያስገኙት ነገር ቢኖር ጥገኝነትና ጠባቂነትን ማስረፅ፣ በሌላ በኩል ደግሞ « የአቤት ባይና አቤቱታ አድማጭ » አካሄድ እንዲያቆጠቁጥ ማድረግ ነው፡፡

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወደ አገራችን ሲገቡ ከመንግስት ጋር በገቡት ውል መሰረት የተለያዩ ተግባራትን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲያከናውኑ እንዲሁም ያለባቸውን ችግር አስወግደው በእድገት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ጉልህ ድርሻ እንዲኖራቸው የሚያስችል የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት የተወካዮች ም/ቤት አፅድቋል፡፡

የአዋጁ አብይ ዓላማዎች ብዙ ቢሆኑም ከሁሉም በላይ ግን የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የቆሙለትን ዓላማ በህግ እንዲወጡ ከማስቻሉ በላይ የግልፅነትና የተጠያቂነት መርህ በአሰራራቸው እንዲሰፍን ያደርጋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በአገራችን ውስጥ ድህነትን በመቀነስና አደጋን በመከላከል፣ የአካባቢ ጥበቃን በማፋጠን፣ የእንስሳትን ደህንነትና ጥበቃን በማስፋፋት ፣ ትምህርትና ጥበብን ፣ባህልና ቅርስን ወይም ሳይንስን በማዳበር፣ስፖርትና የወጣቶች ደህንነትን በማስፋፋት፣የአካልና የአእምሮ ጉዳተኞችን በመታደግና የአገሪቱን ዘላቂ የልማት አቅጣጫ መሰረት በማድረግ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በማበረታታትና በመሳሰሉ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ህግንና የገቡበትን ውል መሰረት አድርገው ሊሳተፉ የሚችሉበት ሁኔታ በአዋጁ ተመቻችቷል፡፡

በዚህ አዋጅ መያዶች ከሚያገኙት ገንዘብ ውስጥ ሰላሳ በመቶ ያልበለጠ ለአስተዳደራዊ ስራ ማዋል እንደሚችሉ በግልፅ ያስቀመጠ ከመሆኑም በላይ፣ አስራራቸውን በግልፅ በሚታይ የሂሳብ መዝገብ መያዝና ኦዲት ማስደረግ እንዳለባቸው ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን ፣በየአመቱ የኦዲት ውጤታቸውንና የስራ አፈፃፀማቸውን ለኤጀንሲው ማቅረብ እንዳለባቸው ደንግጓል፡፡

አዋጁ የውጭ መያዶች በአገሪቱ ፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ መግባት እንደሌለባቸው በግልፅ የተቀመጠ ጉዳይ ሲሆን፣ይህም በአሁኑ ዓለም በኢኮኖሚ በገፉ አገሮች ጭምር ድርጅቶች በውጭ ገንዘብና በውጭ ሀይል ተፅዕኖ ስር እንዳይወድቁ ከሚደረገው አለማቀፋዊ የአሰራር ልምድ ጋር የተገናዘበ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡

ይሁን እንጂ ይህ አዋጅ ከመፅደቁ በፊት ሆነ ከፀደቀ በኃላ የአዋጁን መንፈስና ተግባራዊነት የሚፃረሩ አስተያቶች ሲንፀባረቁ ይታያል፡፡

በዚህ አዋጅ መሰረት በአገራችን ኢትዮጵያ የተቋቋሙ ሆነ ለወደፊት የሚቋቋሙ የቡዙሀን ማህበራት የሚሰባሰቡትና የሚደራጁት በስራቸው ያለውን አባል ጥቅም ለማስጠበቅ በመሆኑ የጥንካሬቸው መሰረቱ ይሄው አባል በሚያበረክተው ሞያ፣ገንዘብና እውቀት ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ ይህ አሰራርም የአገራችን ብዙሀን ማህበራት በራሳቸው የሚተማመኑ እንዲሆኑ የሚያስችል ብቻ ሳይሆን ከውጭ በሚመጣ ተፅዕኖ ስር እንዳይወድቁ ይታደጋቸዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ እነዚህ ብዙሀን ማህበራት ከውጭ የሚያገኙት ገንዘብ ካለ ከአስር በመቶ መብለጥ እንደሌለበት በአዋጁ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ይህም ከውጭ በሚመጣ ንዋይ ምክኒያት የቡዙሀን ማህበራት ሊደርስ የሚለውን ተፅዕኖ ከስር መሰረቱ የሚያደርቅ ከመሆኑም በላይ ፣ብዙሀን ማህበራት በአገር ውስጥ በሚገኝ ሀብትና የሰው ሀይል በመተማመን በዚሁ አኳያ እንዲሰሩ ያደረጋቸዋል፡፡

የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶች በአገራችን ፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ መግባት እንደማይችሉ በግልፅ ተደንግጓል፡፡የፖለቲካ ተሳትፎ በኢትዮጵያ ህገ መንግስት ለኢትዮጵያ ዜጎች የተሰጠ መብት በመሆኑ የውጭ ሀይላት ሊሳተፉበት እንደማይችሉ ዕሙን ነው፡፡ ይህ ከሞላ ጎደል በበለፀጉትም ሆነ በማደግ ላይ በሚገኙ አገሮች ተቀባይነት ያለው አሰራር ነው፡፡ በመሆኑም መያዶች በአገራችን የሚያደርጉት ተሳትፎ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በተደረገ ስምምነት ተመስርቶ የሚከናወን ሲሆን መንግስት እነዚሁኑ አካላት ከተፈቀደላቸው ዓላማ ውጭ ሲሳተፉ ባገኘበት ግዜ ሁሉ ስራቸውን ሊያግድ ይችላል፡፡ ስለዚህ ተሳትፎቸው ህገመንግስታዊ ሳይሆን ከመንግስት ጋር የሚደረግ ስምምነት ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ አገር የፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ የሚያስገባቸው አሰራር ሆነ ልምድ በተለምዶ « የባናና ሪፑብክ» እየተባሉ ከሚታሙ አገሮች ውጭ በየትኛውም አለም የሚታይ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ በሀገራችን ላለፉት ሰላሳ ዓመታት ያለአንዳች ተጨባጭ ህግ የግልፅነትና ተጠያቂነት መርህን በመፃረር ሲከናወን የነበረው የመያዶች አሰራር ወጥ በሆነ ህግ እንዲተዳደሩ መደረጉ በሀቀኛ የበጎ አድራጎት ተግባር የተሰማሩ መያዶችን ያላስከፋ ሲሆን፣ ከቆሙለት ዓላማ ባሻገር ሌላ አጀንዳ የነበራቸውን መያዶች ግን አስቆጥቷል፡፡

ይህ አዋጅ ጥቅማችንን ይነካል ብለው የሚያስቡ ድርጅቶች የኢትዮጵያ መንግስት በሰብዓዊና ዴሞካራሲአዊ መብቶች ዙሪያ እንዳንሰራ እያገደን ነው በማለት እሮሮ ከማሰማት አልፈው የአዋጁን መንፈስ ያልተረዱ አካላት አዋጁን በጥርጣሬ እንዲያዩ ለማድረግ በመሞከር ላይ ናቸው፡፡ እነዚህ ድርጅቶች በአገራችን ህዝብ ስም የሰበሰቡትን ዕርዳታ እንዳሻቸው ለራሳቸው ጥቅም ለማዋልና ከታቀደለት ዓላማ ውጪ ለመጠቀም የሚሹና በአገራችን የፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ መግባት የሚፈልጉ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ መንግስትና የተወካዮች ም/ቤት በዚህ አዋጅ መሰረት ከቀና ዓላማና ከበጎ አሰራር አንፃር አልመው ለሚሰሩ መያዶች መንገዱን ቀና፣ አካሄዱን ለስላሳ በማድረግ ያመቻቹ ሲሆን ፣ግልፅነትን የሚፃረሩ፣ ለሙስና በር የሚከፍቱና ድምር ውጤታቸው በአስተዳደራዊ ወጪ ብቻ የታጠሩ መያዶችን ያገደ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለዚህ የአዋጁ ማዕከላዊ ምህዳር በጎ ራዕይንና ዓላማን የሰነቁ ድርጅቶች በጎ ተግባርን ያከናውኑ ዘንድ የሚያግዝ ፣የሚደግፍና የሚያበረታታ፣በአንፃሩ ደግሞ በበጎ ተግባር ስም የሚያቆጠቁጥ ፖለቲካዊና ርዕዮታዊ ጥገኝነትን ፣ጠባቂነትንና አምላኪነትን የሚገድብ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡